# የሲዖል አርአያ

አንድ ትውልድ መትረው ፤ በልተው የቀበሩ
የደርግ አጋፋሪ ፤ ታጥበው የማይጠሩ
የጨለማው ካህን ፤ የጽልመት ዶክተሩ
የሰው ስጋ በልተው ፤ በደም የሰከሩ
ባለዛር ለቃሊቻ ፤ ዛሬም አልተገሩ
ደም ጠማቸው መሰል ፤ ጮሁብን አጓሩ ።

እልፍ ህጻን የበላ ፤ ጨፍጫፊ ገራፊ
ወላጅን አስለቃሽ ፤ ትውልድን ቀሳፊ
ሺዎችን ያረደ ፤ አንድ ትውልድ አጥፊ
የኢሰፓ ካድሬ ፤ ሆድ አደር ቀጣፊ
ገሎ ሙትን መውቀስ ፤ በዛ አፍ እላፊ
ዛሬም ያቀረሻል ፤ እርካሽ እዳፊ ።

ወጣቱን የፈጀ ፤ ነጥቆ ከናት ጉያ
አስከሬን የሸጠ ፤ አውጥቶ ገበያ
የሰው ማስፈራሪያ ፤ የሲዖል አርአያ
የዲያቢሎስ ወንድም ፤ የጽልመት አምሳያ ።

እውነቱ ይወጣል ፤ መቼም አይቀበር
ህዝብ የበላይ ሲሆን ፤ መጋለጥህ አይቀር
ዛሬም ባይበርድልህ ፤ በብሪት ብትወጠር
እናየው ይሆናል ፤  በሰፈርከው ቁና ፤  አንተም ስትሰፈር ።

ታዛቢው … April 13, 2010